የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥርኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ – ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 63
Addis Ababa 27th July, 2004

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺፮ ዓ·ም
የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ...................................... ገጽ ፪ሺ፰፻፵፪

CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 107/2004
Distribution of Profits of Public Enterprises Council of Ministers Regulation ........................... Page 2842

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺፮
## ስለ መንግሥት የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል
## የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመንግሥት ልማት ድርጅቶች የትርፍ ድልድል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፯/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩· "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፪/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣

፪· "የተጣራ ትርፍ" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፪/፯ የተሰጠው ትርጓሜ ይኖረዋል፣

፫· "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፬፻፲፪/፲፱፻፺፮ የተቋቋመው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ነው።

፬· "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 107/2004
## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DISTRIBUTION OF PROFITS OF PUBLIC ENTERPRISES

The Council of Ministers has issued this Regulaiton pursuant to Articles 5 of the Definition of powers and Duties of the Executive Organs of the Federal democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 4/1994.

1. *Short Title*

   This Regulation may be cited as the "Distribution of Profits of Public Enterprises Council of Ministers Regulation No.107/2004".

2. *Definitions*

   In this Regulaiton:

   1) "Public Enterprise" shall have the meaning assigned to it under Article 2(2) of Proclamation No. 412/2004;
   2) "Net Profit' shall have the meaning assigned to it under Article 2(7) Proclamation No. 25/1992;
   3) "Authority" means the Public Enterprises Supervising Authority establsihed under Proclamation No. 412/2004;
   4) "Ministry" means the Ministry of Trade and Industry.

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>የትርፍ ድልድል</u>

፩· ከመንግሥት የልማት ድርጅት የተጣራ ትርፍ ላይ በአዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፳፱/፪ መሠረት የሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ከተቀነሰ በኋላ የሚቀረው ትርፍ እንደሚከተለው ይደለደላል።

ሀ) ለመንግሥት የትርፍ ድርሻ .................. ፷%

ለ) ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ ........ ፵% ይሆናል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው የትርፍ ክፍፍል ድልድል ቢኖርም ከሚኒስቴሩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚቀርበው የውሣኔ ሃሣብ መሠረት ድልድሉ ሊሻሻል ይችላል።

፫· የመንግሥት የትርፍ ድርሻ በአዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፴፩ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ በቅድሚያ ለመንግሥት ፈሰስ ከተደረገ በኋላ ለኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የተመደበው ገንዘብ ይከፈላል።

፬· <u>የትርፍ መግለጫ ስለማቅረብ</u>

ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ግምት መግለጫ የዘጠኝ ወራት ክንውንና የቀሪዎቹ ሦስት ወራት ግምት መሠረት በማድረግ በበጀት ዓመቱ እስከ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፭· <u>የባለሥልጣኑ ተግባር</u>

፩· ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሠረት የቀረበለትን መረጃ መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የመንግሥት የልማት ድርጅት ዓመታዊ ትርፍና በዚህ ደንብ መሠረት ስለሚደረገው ክፍፍል የተዘጋጀ መግለጫ በበጀት ዓመቱ እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ ባለው ጊዜ ውስጥ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፪· ባለሥልጣኑ በጊዜያዊ የሂሣብ መግለጫ ላይ ተመስርቶ በበጀት ዓመቱ የተገኘውን የተጣራ ትርፍ በጀት ዓመቱ ካለቀ እስከ ህዳር ፲፬ ቀን ድረስ ለሚኒስቴሩ ያሳውቃል። ሆኖም በጊዜያዊ ሂሣብ መግለጫና ትርፍና በኦዲተር በተረጋገጠ ሂሣብ መግለጫ ትርፍ መካከል ልዩነት ሲኖር በውጤቱ ላይ ተመስርቶ ማስተካከያ ይደረጋል።

፮· <u>የፈንዱ ዓላማ</u>

ፈንዱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ለማሻሻል፣ ለማስፋፋት፣ ወይም አዲስ ለሚቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ፕሮጀክቶች ጥናት ማስፈጸሚያ እና ማቋቋሚያ መነሻ ካፒታል ይውላል።

፯· <u>የፈንዱ አጠቃቀም</u>

ፈንዱ መንግሥት በሚያወጣው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት በሚኒስቴሩ እየተፈቀደ ጥቅም ላይ ይውላል።

፰· <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ለማውጣት ይችላል።

፱· <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስቴር

3. *Distribution of Profits*

1. The net profits of a public enterprise shall, after deduction of legal reserve pursuant to Article 29(2) of Proclamation No 25/1992, be distributed as follows:
   a) as dividend to the Government 60%
   b) to the Indistrial Development Fund 40%
2. The distribution of profit may be modified on the basis of a proposal made and submitted to the Council of Ministers by the Ministry notwithstanding the stipulation provided under sub-Article 1 of this Article.
3. After the dividend to the Government is transferred to same within the time limit fixed under Article 31 of Proclamation No 25/1992, the money allocated to the Industrial Development Fund shall be paid.

4. *Submission of Statement of Profit*

Every public enterprise shall submit to the Authority, until the end of April of each fiscal year, a statement on its estimated net profits based on its performance during the preceding nine months and its projected performance for the next three months.

5. *Duties of the Authority*

1) The Authority shall submit to the MInistry, until the end of the month of May of each fiscal year a statement on the annual net profits of every public enterprise and the distribution of the net profits on the basis of information submitted to it in accordance with Article 4 of this Regulation.
2) The Authority shall, based on provisional financial statements, notify the Ministry until November 23 following the end of each fiscal year of the total of the net profits obtained during the fiscal year. Nonetheless, adjustment shall be made should there be difference between the provisional financial statements and audited financial statements.

6. *Purpose of the Fund*

The purpose for which the fund is establsihed is to finance the rehabilitation and expansion of existing public enterprises and to undertake studies of public enterprises to be established and to serve as the initial capital for same.

7. *Utilization of the Fund*

The Fund shall be utilized by the Ministry in Conformity with a directive to be given by the Government.

8. *Power to Issue Directives*

The Ministry may issue directives, which are necessary for the implementation of this Regulation.

9. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force on the date publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 27 day of July 2004

Meles Zenawi
Prime Minister of
The Federal Democratic Republic of Ethiopia